# ፍቅር ለማያልቅ ነገር!

*በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)*

*ትርጉሙ ገብቶንም ሆነ ሳይገባን "ፍቅር" ጠርንፎ ይዞ ያንገላታን ወይም እያሰቃየን ያለን ብዙዎች ነን። መተኛት አቅቶን አይናችን በሩን ሳይዘጋ የሚነጋልን፤ እህል ውሀ አልቀመስ ብሎን መላ ቅጡ የሚጠፋብን በርካታዎች ነን።  አፈቀርን ብለን ልብሳችንን የምንጥለውን፣ ይሉኝታን እንደ ገመድ ቦጭቀን የምንነጉደውን ብዛት እርሱ ይቁጠረው። የፍቅር ሰመመን ቆሰቆሰን እያልን ለብቻችን ሆነን አንገታችንን እያወዛወዝን የምናንጎራጉር አለን። ወላጅ እንደሞተበት ስቅስቅ ብለን የምናለቅስም ሞልተናል። በፍቅር እያመካኘን ያልሆነውን ነን እያልን ራሳችንን እየካብን የምንደሰኩረውን ብዛት አንባቢ መገመት ይችላል። ፍቅርን ፍለጋ ወይም ፍቅር እንደ በጋ ቀትር ወግቶን አካላችንን በጌጣ ጌጥ አሽቆጥቁጠን ወይም እንደ አገረ ገዥ ዶሮ ወጥ በቅባት ነክረን ወዲያ ወዲህ ስንል የምንውለውን ቁጥር ሆድ ይፍጀው ብለን እንለፈው።*

*ስለፍቅር ያልተዘፈነ ዘፈን፣ ያልተከረከረ መሰንቆ፣ ያልተመታ ክራር፣ ያልተወቀረ ከበሮ፣ ያልተንቆረቆረ ዋሽንት ያለ አይመስልም።  ስለ ጸጉር ዞማነት፣ ስለአይን ዛጎልነት፣ ስለ ጥርስ ንጣት፣ ስለአንገት መቃነት፣ ስለ አፍንጫ ስንደዶነት፣ ስለደረት ስፋት፣ ስለወገብ ቺቦነት፣ ስለደም ግባት፣ ስለባት አቀማማጥ ያልተዘፈነ ዘፈን ያለ አይመስለኝም።  ሌላው ሳይቀር ስለጆሮና ስለጥፍር ውበትም ድርሰት ተደርሷል። ዜማም ተቀነባብሯል። ከቁሳዊ ገላ አልፎ ሰው አረማመድን፣ አቀማመጥን፣ አነጋገርን፣ አበላልን ሁሉ ያፈቅራል። የአረማመድ፣ የአነጋገር ወይም የአበላል እንከን አላት ወይም አለው እየተባለ የትዳር ጓደኛ ለማግኘት የተቸገረውን የቆጎዳ ልብ ያውቀዋል። ብችል ማውቅ የምፈልገው ግን አንዱ ቀለም ከሌላው፣ ይኸኛው መልክ ከዚያኛው ወይም አንዱ አይነት አረማመድ ወይም አበላል ከሌላው ያመረ መሆኑን ማን እንደወሰነ ማወቅ ነው? አዎ አስር ቁጥር ወገብ ከአርባ፤ ለቀቅ ያለ አፍንጫ ጉርድ ካለችዋ ያምራል ብሎ ማን ደነገገ? ቀውላሌ ከድንክዬ፤ ሸንቃጤም ከቸንቧሌ ያምራል ብሎ ፍርድ የሰጠ ማን ይሆን?*

*ላጤነው ከላይ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ የተመረኮዘ ፍቅር ቢያንስ ሁለት ባህሪዎች አሉት። አንደኛው ባህሪ አንጻራዊነቱ ነው።  በአካል ላይ የተመሰረተ ፍቅር አንዱን አካል ከሌላው ጋር ከማወዳደር የመነጨ ነው።  ቀዩን ከቀይ ዳማው፤ ቀይዳማውን ከጥቁሩ፤ አጭሩን ከረጅሙ ወዘተ ጋር ከማወዳደር የሚነሳ ነው። አንደኛው ከሌላው ያምራል ብሎ የወሰነውን ዳኛ የማወቅ እድል ቢኖረኝ ኖሮ በምን ምክንያት ላይ ተመስርቶ ይህን ፍርድ እንደሰጠ ብጠይቀው ደስ ባለኝ ነበር። ሁለተኛው ባህሪ ደግሞ ጊዚያዊነቱ  ነው። በጥርስ ላይ የተመሰረተ ፍቅር ጥርስ አቶ ድድን ደህና ሰንብት በማለት እየሾለከ ከፊት ላይ ዱብ ቢል ወይም ደግሞ ከዚያው ተተክሎ መልኩ ቢወበይ የፍቅር ጥርስም ስሩ ይነግላል ወይም መልኩን ይቀየራል።  ችቦ ወገብ ላይ የሰፈረ ፍቅር እንደዚሁ ቦርጭ ከፊት ለፊት ሄዶ ይሉኝታውን ጥሎ ዝርፍጥ ሲልበት ይጠፋል። ታዲያ ለመሆኑ እነዚህ ሁለት ባህሪዎች የሌሉት ፍቅር አለን?*

*ነፍሳቸው እስከምታልፍ ወይም ተገፍትረው እስከሚወድቁ በጥርስም በድድም ሕዝብ በሚነክሱ ገዥዎች ስር ለኖርነውና በመኖርም ላይ ላለነው የገንዘብና የስልጣንን ፍቅር እስከለተሞት ቆርንኖ የሚይዝ ተወዳዳሪ የሌለው ፍቅር አድርገን ልንገምት እንችላለን። በደንብ ከተስተዋለ ግን  ከአንድ እንጀራ በላይ ተበልቶ ይታደር ይመስል ዛሬ እንኳን በሃያ አንደኛው ክፍለ-ዘመን ህጻናት የርሃብን ለቅሶ እያለቀሱ ጊዜ ከሰጠኝና በለስ ከቀናኝ ብሎ ያገር ሐብትን እያግበሰበሱ ከኪስ መክተት የበሽታ ምልክት እንጅ የፍቅር ገጽታ አይደለም። እርግጥ ነው በገንዘብ ስስት ንብረት ለመስረቅ ከሰው ቤት ሲገቡ በመጥረቢያ ሳይቀር የራስ-ቅላቸውን የሚፈረከሱ አያሌ ናቸው። ለገንዘብ ሲሉ የሰውን ህይወት የሚያጠፉ ስፍር ቁጠር የላቸውም። ለገንዘብ ሲሉ ምህረት-የለሽ ገዥዎችን የሚያገለግሉ፣ እየዋሹ እየቀጠፉ ሰላማዊ ሰውን የሚያሳስሩ፣ የሚያስገድሉ፤ ለገንዘብ ሲሉ አገዛዝ ወንበር ላይ ቁጢጥ ብለው የንጹሐንን ደም እንደ ጅረት የሚያፈሱ አንድ ሁለት ተብለው እንደማያልቁ "እህህ" እያለ  በሆዱ እያመቀ ችሎት የሚኖረው መከረኛ ሕዝብ ሁሉ ያውቀዋል። ነገር ግን ይህ ልክፍተ-ገንዘብ እንጅ ፍቅረ-ንዋይ አይደለም።*

*የስልጣን ቆሌም ተመሳሳይ ነው። እንዲያውም የስልጣን ስስት የሚያመጣውን ጣጣ ለጦቢያ ልጆች መንገር ያልበረደውን ሐዘናቸውን ይበልጥ ማንፈቅፈቅ፤ የባሰም ማስገንፈል ነው። ለስልጣን መስገብገብ ከሰው በታች ከሚያደርግ የቅኝ አገዛዝ ጣጣ ያዳኑንን ጀግኖች ሳይቀር አስገድሏል። የስልጣን ዛር አገር ተረካቢ፣ የምርምር፣ የአዲስ ግኝት ምንጭ የሆነውን ወጣት አሳጭዶ እናቶች እንዳያለቅሱ ከልክሏል። የስልጣን አቴቴ እንደመረብ ተጠላልፎ የተሳሰረ ሕዝብ በግድ ከፍሏል። ርስብርሱ ሲናከስ እንዲኖርም ለማድረግም በልሳኑ ከፋፍሏል። የስልጣን ስስት አዛውንቱን ወጣቱን ከወህኒ ዶሏል። የስልጣን ጋኛ የስንቱን ህይወት ቀስፏል። ወላጅን ልጄ ልጄ፣ ልጅንም እናቴ አባቴ እያለ እንዲያለቅስ አድርጓል እያደረገም ነው። ደጉ ነገር ግን ሁሉም ነገር እንደ ጤዛ አላፊ መሆኑ ነው። የጊዜ ጉዳይ እንጅ ሕዝብን ሁሌ ጥቁር ለባሽ፤ ዘወትር ሐዘንተኛ አርገውት የሚኖሩትም ቢሆን እንደ ካፊያ አላፊዎች ናቸው። ሕዝብ ለጥ ገጥ ብሉ ቢገዛ እርጅናና ሌሎችም የተፈጥሮ*

ሂደቶች ስራቸውን አይፈቱም። የነዚህ አይነት ሰዎች ሁኔታ ሲታሰብስ እንኳንም እርጅና፤ እንኳንም ሞት፣ እንኳንም ዘላለም አለመኖር አለ። እነዚህ ነግሮች ባይኖሩማ በስልጣንና በገንዘብ ሥነ-ልቡናቸው ጥቅጥቅ ብሎ የታፈኑት ጉዶች በቶፋ እየቀቀሉ አይበሉንም ነበርን? አዎ እንኳንም ማለፍ አለ! እንኳንም በድሃ ጉረሮ እንጨት እየሰደዱ ሲያግበሰብሱ የኖሩትን ንብረት ትቶ መሄድ አለ። እንኳንም ገዳዮች ካለእድሜቸው መቃብር ውስጥ ከሚያስገቧቸው ሙታን ጋር የመገናኘት እጣ ፈንታ አላቸው።

ሰው አዲስ አመት በመጣ ቁጥር ብዙ ተስፋ ይመኛል። መኪና፣ ቤት፣ ልብስ፣ የትዳር ጓደኛ ወዘተን ያልማል። ተገደው ርሃብ የእለት ከእለት ኑሯቸው ከሆኑትም ገሚሶቹ  ለአንድ ቀን እንኳን የቅቤ ሽሮ ቀምሰው ለማደር አምላክን ሲለምኑ፤ ዙፋን ላይ ተቀምጠው ችጋርን እንደናዳ በሕዝብ ላይ ከሚለቁት ባለስልጣናት ክፊሎቹ ደግሞ ስልጣናቸውን እንዲጠብቅላቸው ወይም ከፍከፍ እንዲያደርግላቸው ገብስማ ዶሮ አርደው ሲያዞሩ ሊታዩ ይችላሉ።  ከተሞክሯችን እንዳየነው የሰው ህይወት በስለት መልክ የሚያቀቡ አይኖሩምም አይባልም። የማይሆን ምኞት ብላችሁ አትጠቃቀሱብኝ እንጅ እኔ እምመኘው ሟችን ገዳይ በሆዱ በማይገዛ፣ በአይን ጥቅሻ ወይም በስልክ በማይታዘዝ የእውነተኛዋ ካባ ለባሽ፣ ፍጹም ከሆነው ከሰማይ ቤቱ ዳኛ ፊት ቀርበው እውነተኛዋን ፍርድ ሲቀበሉ ማየት ነበር። ነፍሰ-ገዳዮች ሲኖሩም እየተቅበዘበዙ የሚኖሩ ፍጡራን ናቸው። እንኳን የብዙሐንን የአንድን ሰው ነፍስ ያጠፋም በሰላም ይኖራል ሲባል ሰምቼ አላውቅም።  ከላይ እንደተጠቀሰው በፍጡራን መልክም ተሰርተዋልና እንደማንኛችንም መሞታቸውም አይቀሬ ነው። ሳይሞት የሚቀር ሰው አለ ሲባል እንኳን ከሌላ እንደ ጥርስ ሳሙና(toothpaste) አፍረጥርጠው ቢጨምቁት እንኳን እውነት ጠብ ከማይለው፤ ሰማእቱ አቡነ ጴጥሮስ ከመሞት በኋላ እንኳን በሰላም እንዳይኖሩ ከአጠገባቸው ሆኖ ነጋ ጠባ ከሚያደነቁራቸው ማስታወቂ(ማደናሪያ) ሚኒስቴርም እስካሁን አልሰማሁም። ስልጣንና ገንዘብ እንደቆሌ ከገኘሮዎች ናላ ላይ እየሰፈሩ ካለኮርቻ እንደጋለቧቸው፣ አለም የያዘቻቸውን ሐጥያቶች ሁሉ እንዳሰሯቸው ይኖራሉ። ስለዚህ  በእደዚህ አይነት ሰዎችና በስልጣን ወይም በገንዘብ መካከል ያለው የጠበቀ ግንኙነት የፍቅር መልክ ያለው ሳይሆን የዝሁል-ህሊና ቀውስ ወይም የቃልቻ አይነት መልክ ያለው ነው።  ታዲያ አንጻራዊ ባህሪ የሌለው ወይም ጊዜ ማይወስነው ፍቅር ከምን ይመነጫል? በእኔ እምነት አያሌ ከሆኑት የጽሑፍ አላማዎች አንዱ አንባቢ እንዲያስብ፣ የራሱን አእምሮ እንዲፈትሽ፣ እንዲከራከር ወዘተ ማድረግ ነው። ከላይ ለተጠየቀው ጥያቄ እያንዳንዳችን የየራሳችን ወይም ተመሳሳይ መልስ ሊኖረን ይችላል። አንባቢ የሚያስበውን ያስብ እኔም የምለውን ልበል።

በኔ አመለካከት ከጥንታዊው የአንጎል ክፍል(primitive brain) እና ከላቀው አንጎል (transcended brain) የሚመነጭ ፍቅር አለ። የፊተኛውን ከሌሎች እንሰሳት ጋር ስንጋራው የኋለኛው ለሰው ልጅ የተሰጠ ጸጋ ብቻ ነው። (1) የወላጅና የልጅ ፍቅር በእንሰሶችም አለ። እንደኛ ድል ያለ ድግስ ደግሰው አይጋቡ እንጅ ተቃራኒ ጾታዎችም ለኛ ባይገባንም ፍቅር አላቸው። እንሰሳት ለሚበሉትና ለሚጠጡት ነገርም ይሳሳሉ፤ ይሻማሉም። ነገር ግን የላቀው የአእምሮ ክፍል ስለሚጎላቸው ማሰብ መመራመር አይችሉም። የላቀ አንጎል ሳይኖራቸው ከላቀ የአእምሮ ክፍል የሚመነጭ ፍቅር ሊኖራቸው አይችልም ማለት ነው። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ተወዳዳሪና የጊዜ ውስንነት የሌለው ፍቅር ለማለት በመዳዳት ላይ ያለሁት ከዚህ ከላቀው የአእምሮ ክፍል የሚመነጨውን ፍቅር ነው።

የዳበረ አእምሮ ከሚሰራቸው በርካታ ክንውኖች ጥቂቶቹ አካባቢን መፈተሽ፣ መመራመርና መፈላሰፍ ናቸው። ፍላስፋዎች ፍልስፍናን ፍቀረ-እውነት (Philosphy = love of wisdom; phil = love) ይሉታል። (2) ፍልስፍና ከጥንታዊው የአእምሮ ክፍል ስለማይመጣ ለእውነት ያለ ፍቅርም ከጥንታዊው የአእምሮ ክፍል አይመነጭም። ክርስቶስ ለእውነት ሲል የተሰቀለው እንደዛሬ መነኩሴዎች ምእመናን በምድር ገሃነብ-እሳት የሚጠብሱ ገኘሮዎችን በከበሮ እያወደሰ፣ የስለት ገንዘብ እየበላ፣ ለፈሪሳውያን እያገለገለ መኖር ቸግሮት አይመስለኝም። (3) ሶቅራጥስ ቃሉን ከመዋጥ መርዙን መጠጣት የመረጠው ሕዝብን እየፈጁ የሚኖሩትን እግር እያጠበ እንጀራ መብላት አቅቶት ነው ሊባል ይችላል ብዬ አላምንም። ወይም ደግሞ በጮሌ ቋንቋ ለመግለጽ “ጥሬ” ወይም “ፉራ” ሆኖ አይመስለኝም። (4) ሁለቱንም ያስገደላቸው እኛን ተራ ሰዎችን ብዙም የማይነካን ነገር ግን እነሱን ውጧቸው የነበረ ላቅ ያለ ፍቅር ነው። ከእውነት የመነጨ ፍቅር። ተወዳዳሪ ሆኖ የሚቀርብ ነገር የሚመሳሰል ነገር ነው። እውነትን የሚመስል ነገር የለም።  ተወዳዳሪ ማለት ተቃራኒ ስላልሆነ ቅጥፈት(ሐሰት) እውነትን አይደራደርም። በዚህም ምክንያት ሐሰትን በሰማንያ ብቻ ሳይሆን በሶስት መቶም  አግብተን ያማረ ቀሚስ እያለበስን ስናሽሞነሙናት የምንውለው ሁሉ እውነትን ከሐሰት ጋር ለማወዳደር ስንከጅል ጉረሯችንን ያንቀናል። ከዚህም በተጨማሪ እውነት እንደ ጥርስ ስለማትወልቅ፣ እንደአይን ስለማትደፈርስ፣ ስለማታረጅ፣ ስለማታፈጅ ከርሷ የሚመነጨው ፍቅርም እምቡጥ እንደሆነ ይኖራል። ዳሩ ግን እውነትን የወደደ በምድር አበሳው ብዙ ነው። እውነት በአፍቃሪዎቿ ጎን ተሽጣ፣ ከልባቸው ተጣብቃ፣ በአእምሯቸውም ሰርጸ ስታንገላታ ኖራ በመጨረሻም ታስጠፋለች። የማታ ማታ ግን እርሷ የማታረጅ፣ የማታፍጅ እንደሆነች ሁሉ ፍቅረኞቿን ሁሉ ተደርሶላቸው፣ ተተርኮላቸውና ተዘፍኖላቸው የማይጠገቡ የዘላለም እሸቶች ታደርጋቸዋለች።

ማህተመ ጋንዲን፣(5) ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኔርን፣(6) ኔልሰን ማንዴላን(7) እንኳን የመስዋእትነታቸው ተጠቃሚ የሆነው የኔቢጤ፤ ዛሬ ዛሬ ያሰቃዩአቸውም ሆነ ያስገደሏቸው ሳይቀር በመልካም ያነሷቸዋል። ህያው ተግባራቸውም ለዘላለም ሲነሳ ይኖራል። በእኛም አገር እነአቡነ ጴጥሮስና እነህዲስ አለማየሁ ተደጋግመው ይነሳሉ። እስከማውቀው ድረስ ባለንበት ዘመን ማንም ስለነዚህ ሰዎች ነቀፋ ሲያነሳ አይሰማም። እነዚህን ሰዎች የሚያመሳስላቸው ከብዙዎቻችን ዘንድ የጎደለ በነሱ ግን የሞላ ላቅ ካለው የአእምሮ ክፍል የሚመነጭ ፍቅር ነው። የሕግ ምሁሩን ጋንዲን የአገሩን ሕዝብ በተፈጠረበት ምድር አገልጋይ አርገውት ይኖሩት የነበሩት በሴት፣ በገንዘብና በስልጣን ሊገዙት ሞክረው ነበር። ፍትህን አግብቶ ይኖር ስለነበር ለፍትህ ያለው ፍቅር እንኳን እርሱን በዘመኑ የነበረውንም ሆን ከዚያ በኋላ ለዘላለም ወደፊት የሚኖረውን ያገሩን ሕዝብ ሌጣ አገልጋይ ከመሆን አድኖታል። ማርቲን ሉተር ኪንግም ለፍትህ የነበረው ፍቅር ለራሱ አካላዊ ኑሮ ሳይመች ቢቀርም ዛሬ እንደ ጀግና ጠጉራችንን አንጨብረን፣ ሎቲ አንጠልጥለን በአሜሪካ ምድር ለምንሽቀረቀረው ሳይቀር ጠቅሟል። ለአስርተ አመታት ከፍትህ ጋር ታስሮ የነበረው ማንዴላ ወደር የሌለው የፍትህ ፍቅረኛ መሆኑን ከማንኛውም የግፍ-ቋት ከሆነ አፍሪካዊ ገዥ በተለዪ መልኩ በሕዝብ የተሰጠውን ስልጣን ተረከቡ ብሎ ያስረከበ እለት አስመስክሯል። አባታችን አቡነ ጴጥሮስ ዛሬ እንደምናያቸው ካባቸውን እያሳመሩ፣ የሕዝብን የስለት ገንዘብ ጥሽቅም አርገው እየበሉ ነገር ግን የብጹአን ህይወት እንደ ቅጠል ሲረግፍ ጸሎት እንኳን እንደማያደርሱ ጳጳሳት አለመኖርን መርጠዋል። የደርቡት የፍትህ ካባ፣ ያጠለቁት የእውነት ቆብ ሕይወታቸውን ይዞት ሄዷል። “አራዳ” ጳጳስ፣ አሙለጭላጭ ወይም ዘበናይ መነኩሴ መሆን አቅቷቸው አይመስለኝም። (8) ክቡር አቶ ሀዲስ አለማየሁ  በዘመናቸው እንደነበሩት ፊደል ቆጣሪዎች ገዥን እያወደሱ፣ ምን ልታዘዝ እያሉ፣ የድሃን ገንዘብ እያግበሰበሱ በየመሸታ ቤቱ እየጨፈሩ፣ በየመንደሩ እቁባት እያስቀመጡ ከመኖር ወይም ከመሰደድ ፋንታ ተዋግተው ሕዝብን ከቅኝ አገዛዝ ውርደት ለማዳን በአንድ እጃቸው ጠመንጃን  በሌላው ብዕርን ጨብጠው ተዋግተዋል። ሰሚ ቢያጡም እስከሚሞቱባት ዘመን ድረስ እጃቸው እስከሚደማ እንቅልፋቸውን አጥተው ስለሚወዱት ፍትህ እንደጻፉ፤ እንደተናገሩ አልፈዋል። (9) ሰውን በሕይወት እያለ ማመስገን ብዙውን ጊዜ ተዋጥቶልን አያውቅም እንጅ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያምም የፍትህ ፍቅረኛ ናቸው ብዬ አምናለሁ። (9) የፍትህን ወዳጆች የሚወልዳቸው ኢፍትሐዊነት ነው። ይህ ማለት ግን ኢፍትህዊነት የፍትህ ተወዳዳሪ ነው ማለት አይደለም። ቅጥፈት(ሐሰት) የእውነት ተቃራኒው የሆነውን ያህል ኢፍትሃዊነትም የፍትህ ተቃራኒ ነው። በተመሳሳይ መንገድ እንደ እውነት ሁሉ ፍትህም ተወዳዳሪ የላትም። ፍትህና እውነት ግን አንድ አይደሉም። ፍትሐዊ የሆነ ጉዳይ ሁሉ እውነት አይደለምና።

የሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቶች ምግብ መጠጥና መጠለያ እንደሆኑ ይወሳል። ልብ ብላችሁ እዩልኝ። እነዚህ በእውነቱ ለጉንዳኑንም፣ ለፍየሏም፣ ለጅቡም ሆነ ለሌሎች እንስሳት ያስፈልጋሉ። ይልቁንስ የሰው ልጅ እንደሰውነቱ ከእነዚህ በላይ የሆነ ፍትህ የሚባል መሰረታዊ ፍላጎት ያሻዋል። ቢርበው፣ ቢጠማው፣ መንገድ ዳር ቢያድርም ሰው ፍትህን እስከለበሰ ድረስ ያው ሰው ነው። መብት የሌለው ሰው ከበላ ከጠጣ እንስሳ፣ ሁሉንም ከነሳው ደግሞ ከዚያም በታች ነው። ዳሩ ግን ለተወሰነ የህብረተሰብ ክፍል ብቻ ፍትህን መጠየቅ ፍትህ ፈላጊ አያሰኝም። እንዲያውም እንዲህ አይነቱ አኪያሄድ ለሌላው የህብረተሰብ ክፍል ደንታ የለኝም አይነት መንገድ ስለሆነ የኢፍትሐዊነትን አድማስ ያሰፋዋል። ፍትህ ቡድንም ሆነ ድንበር የለውም። የዚህኛው ቋንቋ ተናጋሪ ፍትህ የዚያኛው ጎሳ ፍትህ ብሎ ነገር የለም። ፍትህ “ወርዶ ጠባብ ነው አትወጥሩኝ” አይልም። ፍትህ ዘር፣ ቋንቋ፣ ጾታ፣ እድሜም ሆነ ክልል አያውቅም። የሰው ልጅ የጣእም ቃና ይለያያል። እንደኔ እንደኔ የፍትህ መዓዛና ጣእም ከማር ከወተትም ይጥማል።  ፍትህ ሲውል ሲያድር መልክ ወይም ሽታ አይቀይርም። ፍትህ ለሰው ልጅ ህይወት ዋና ቁልፍ(master key) ነው። ፍትህ የትውልድን አእምሮ ቡኣ አርጎ ይከፍታል። የትምህርትን፣ የንግድን፣ የእርሻና የሌሎችንም የማህበረሰብ ክንውኖች ያፋፋማል። ፍትህ ችጋርን እንደ አረም ነቅሎ ይጥላል። ፍትህ በሽታን ይከላከላል፤ ይፈውሳል። ፍትህ የደስታ፣ የፍቅር፣ የመተሳሰብና የመተሳሰር መሰረት ነው። ፍትህ ከተከሉትና ከኮተኮቱት ሁሌ እሸት፣ ሁሌ አበባ ነው። ቀምሰው ካጣጣሙት የፍትህ ፍቅርም እንደ ፍትህ ጣፋጭ ነው።

ለማጠቃለል ያህል ፍጡራን እንደመሆናችን መጠን ለተክለ ቁመና ፍቅር፣ ለዘፈን ፍቅር፣ ገንዘብንና ስልጣንን ባግባቡ የመጠቀም ፍቅር ሁሉ አስፍላጊ ናቸው። እነዚህ ከሌሉ ማህበረሰብ በማህበረሰብነቱ ለመቀጠልም ይቸገራል። ነገር ግን ሰው ጭራሹን ከእውነት ከራቀ፣ መብት ከሌለውና ፍትህን ከተነሳ ሰውነቱ ይሸረፋል ወይም ያከትማል። የምንበላ የምንጠጣ፤ አውቶሞቢል የምናሽከረከርንም ሆነ ቪላ ቤት ውስጥ የምንኖር ዳሩ ግን መብታችን በሰው እጅ የሆንና ከፍትህ የራቅን ሰዎች ሁሉ “በእንሰሳት መጠበቂያ (Animal Zoo) ውስጥ ህክምናን ጨምሮ እንክብካቤ እየተደረገላቸው ከሚዝናኑባቸው የሜዳ አህያና ግመል ምን ይለየናል?” ብለን እንጠይቅ። ሹመት በመሰጠቴ፣ ላቦራቶሪ ውስጥ መስራት በመቻሌ፣ሐኪም፣ መሀንዲስ ወይም የሕግ ባለሙያ በመሆኔ ፣ ቱጃር ነጋዴ በመሆኔ፣ ወዘተ እያልን ራሳችንን አናታል። ከአነስተኛ ፍጡራን በምንጋራው የፍቅር ባህሪ ሙሉ በሙሉ እየተጠልፈንም የሰው መለያ የሆነውን ፍቅር አንርሳ። አዎ እንደሰው ሆኖ ለመኖር ወይም እንደህብረተሰብ ለመቀጠል ፍቅር ለማያልቅ ነገር!  አመሰግናለሁ።

*ዋቢ*


1. *ደግነትና ክፋት ምንድን ናቸው (ለማንበብ ይህን ይጫኑ* *http://addisvoice.com/article/Good.pdf )*
2. *Coffee with Plato* by *Donald R. Moor*, *Robert M. Pirsig* , 2007
3. *የሆሐንስ ወንጌል-መጽሐፍ ቅዱስ*
4. *The Republic,* by *Plato*, *Grube G. M. A.*, 2002
5. ***The Essential Gandhi: An Anthology of His Writings on His Life, Work, and Ideas by Mahatma Gandi, Lousi Fisher, 2002***
6. *The Autobiography of Martin Luther King, Jr.* by *Martin Luther King, Jr.*, *Clayborne Carson* (Editor) 2001
7. *Nelson Mandela, Reggie Finlayson, 2005*
8. *ድንጋይን የሚያናግረው ውኃ ነው (ለማንበብ ይህን ይጫኑ http://addisvoice.com/article/dengay-2.pdf)*
9. *ከሰማእታትና ከሐዋርያት ለመረከብ የከበደን ጸጋ (ለማንበብ ይህን ይጫኑ http://addisvoice.com/article/Tsega.pdf)*


**ጥር ሁለት ሺህ ዓ.ም.**